የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party(EPRP)

መስከረም 2/2002

# ኢሕአፓ ለቀድሞ የወንጂና መተሐራ የስኳር ፋብሪካ ሠራተኞች ዳግም ድጋፉን ይሰጣል

የወንጂና የመተሐራ የስኳር ፋብሪካ ሠራተኞች መብታቸወን ለማስከበር እያካሄዱ ላሉት ትግል ድጋፍ በመጠየቃቸው ኢሕአፓ ዛሬም እንደ ትላንቱ ሙሉ ድጋፉን እንደሚሰጣቸው ይገልፃል። በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥት የተቋቀሙት የወንጂ፥ ወንጂ ሸዋና መተሐራ የስኳር ፋብሪካዎች የተመሰረቱበት ቦታ ድንጋዩና ፍልውሃው ፍሎራይድ የሚባል ለሰው አደገኛ የሆነ ንጥረ ነገር የሞላው መሆኑን ሠራተኞቹ አያውቁም ነበር።

የስኳር ፋብሪካዎቹን በማቋቋምና በማካሄድ ሀላፊ የነበረው የሆላንዱ ኤች.ቪ.ኤ ዓለም አቀፍ ተቋም ሲሆን የዚህ ድርጅት ዜጎች ለብቻቸው በአጥር በተከለለ ቦታ በቪላዎች በምቾት ሲኖሩ ውሀቸውም እየተጣራ ከፍሎራይድ ነፃ ይሆን እንደነበር ሊታወቅ ተችሏል። የሆላንድ ባለፋብሪካዎች ዘረኛና ጨካኝ በዝባዥ ስለነበሩም (የአገዳ ቆራጮች የቀን ደሞዝ አንድ ብርም አይሞላም ነበረ) የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ የሀገር ሉዓላዊነትና የሕዝብ መብት መከበር ጥያቄው አኳያ ሲያነሳቸው ከነበሩት ክስተቶች አንዱ ነበር። የስኳር ፋብሪካ ሠራተኞችም የኢትዮጵያ ሠራተኛ ሕዝብ ትግል አካል ሆነው ታግለዋል። በአረመኔው ደርግ ጊዜም የፋብሪካው ሠራተኞች መስዋዕትነትን ከፍለዋል። በገዛ ሀገራቸው ለጭፍንና ምህረት አልባ ብዝበዛ መጋለጥ ብቻ ሳይሆን በአፀያፊ ዘረኝነትም ሊጠቁ የተዳረጉት የስኳር ፋብሪካዎቹ ሠራተኞች በፍሎራይድ የተሞላ ውህን ሲጠጡ በመቆየታቸው ለአጥንት በሽታ ተጋልጠዋል። የፋብሪካው ጢስናጋ ዝም የብዙዎቹን ሳንባና የመተንፈሻ አካላት አበላሽቷል። ሆላንዶቹ ውህን ከፍሎራይድ ማጥሪያ ሁለት መሳሪያዎች በራሳቸው ሽቦ ግቢ (ለነሱ መኖሪያ ብቻ ተብሎ የታጠረ ቦታ ላይ) ሲተክሉ የፍሎራይድ መኖርን ለ17 ዓመት ለኢትዮጵያውያን ሳይገልጡ ሠራተኛውን ሕዝብ ለዘላቂ በሽታና ጉዳት አጋልጠዋል። ይህን ጥፋቱን ኤች.ቪ.ኤ እስከዛሬም አልቀበል ብሏል።

ሽባ የሆኑት ሠራተኞች፤ ቀን ተቀን በሥቃይ እየኖሩ ያሉትና ፊታቸውም የተበለሻሸው ሠራተኞች እየተቀበሉ ያለው መከራ በቀላሉ የሚገመት አለመሆኑን ተጠቂዎቹ ራሳቸው ገልፀዋል። ሰው ፊት ሊቀርቡ ወይም ትዳር ሊመሰርቱ ያልቻሉ ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም። የአልጋ ቁራኛ የሆኑ ብዙዎች ናቸው። ሕፃናትም እግሮቻቸው ሽባ ሰለሆኑ ትምህርት ቤት መሄድ አቅቷቸው ትምህርት አቋርጠዋል። የወንጂ ሠራተኞች ጡረታ አበል ከ48 እስከ 300 ብር በመሆኑም እንኳን ለአስፈላጊው መድሀኒት መግዣ በዚህ ባለው የኑሮ ውድነት ጊዜ ለቤተሰብም ቀን ተቀን ኑሮ በቂ ሆኖ አልተገኘም። የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያ ሠራተኞችን የቻይና ቀጣሪዎች እንዲደበድቡ መብት የሰጠ፤ የሱዳን ወታደሮች የሀገራችንን

መሬት ወረው አርሶ አደሩን እንዲያስሩና እንዲገድሉ የፈቀደ ፀረ ኢትዮጵያ አገዛዝ ነውና ለወንጂ ሠራተኞች ሰቆቃ ግማሽም ጆሮ አልሰጠም።

ኢሕአፓ የስኳር ፋብሪካ የቀድሞ ሠራተኞች በኤች.ቪ.ኤ ላይ የሚያቀርቡትን ክስ ሙሉ በሙሉ ደግፎ ይህ የሆላንድ ኩባንያ ለተጎዱት ሠራተኞችና ቤተሰቦቻቸው ተገቢውን ካሳ እንዲከፍል ይጠይቃል። ሠራተኞቹና ቤተ ሰባቸውም በቂ ህክምናና እንክብካቤን ያገኙ ዘንድም ሙሉ ጥረት መደረግ እንዳለበት ለዜጎች ሁሉ እያሳሰበ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት አሰከባሪ ተቋሞች የስኳር ፋብሪካ ሠራተኞችን ጩኸት እንዲያስተጋቡ ኢሕአፓ ጥሪ ያደርጋል።

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France